# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 120/2014

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ክፍል 1 ....5
ጠቅላላ ድንጋጌ ....5
1. አጭር ርዕስ ....5
2. ትርጓሜ ....5
3. የተፈጻሚነት ወሰን ....7
4. የጤና ሙያ የሥነ-ምግባር ኮሚቴ የተቋቋመበት ዓላማ ....7
5. መሰረታዊ መርሆች ....7
ክፍል ሁለት ....8
የኮሚቴው ተግባር ሃላፊነትና አደረጃጀት ....8
6. የኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነትና ....8
7. የኮሚቴ አደረጃጀት ....9
8. የዋና ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ አመዳደብ ....9
9. የዋና ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት ....9
11. የኮሚቴው ፀሃፊ አመዳደብ ....10
12. የፀሃፊ ተግባርና ኃላፊነት ....10
13. የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ....10
14. የኮሚቴ አባላት ግዴታዎች ....11
15. በኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ....11
16. የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ....11
17. የኮሚቴ አባላት አመራረጥ ....12
18. ኮሚቴ የሚፈርስበት ሁኔታዎች ....12
19. የኮሚቴው ሰብሳቢ ፣ ም/ሰብሳቢና አባል ከስብሰባ የሚነሳበት ወይም ተሳታፊ የማይሆንበት ሁኔታ ....12
20. ከአባልነት ስለማገድ ወይም ስለማሰናበት ....13
21. ስለ ንዑስ ኮሚቴዎች ....13
ክፍል ሶስት ....14
ሰለ አቤቱታ አቀረረብ ምርመራና የውሳኔ ሃሳብ አሰታጥ ሥነ-ሥርዓት ....14
22. የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ....14
23. የቅድመ ማጣራት ሂደት ....14
24. ክስን ስለመከላከል እና እንዲነሳ ስለመጠየቅ ....15
25. አቤቱታ ወይም የመከላከያ መልስ ስለማሻሻል ....16
26. አቤቱታ ስለማንሳት ....16

27. መጥሪያ ስለመላክ ....16
28. አቤቱታ ስለመመርመር ....16
29. ጉዳዩ በሚታይበት እለት አቤቱ አቅራቢው ወይም አቤቱታ የቀረበበት አካል መቅረት ....17
30. ስለ ምስክሮች ....17
31. ሌሎች ማስረጃዎችን ስለመቀበልና ስለመመርመር ....18
32. የውሳኔ ሃሳብ እና አፈጻጸም ....18
33. አስተዳደራዊ እርምጃዎች ....19
34. ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃዎች ....20
35. ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ....21
36. በባለሙያው ላይ የተወሰደው የሥነ-ምግባር አስተዳደራዊ እርምጃ በሪከርድነት የሚጠቀስበት ጊዜ 21
37. ይግባኝ ....21
ክፍል አራት ....22
የተለያዩ ድንጋጌዎች ....22
38. የኮሚቴ አባላት ክፍያን በሚመለከት ....22
39. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች ....22
40. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ....22

## መግቢያ

- የአዲስ አበባ የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ግልጽ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባርና ኃላፊነቱን መወጣት በሚችል መልኩ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- የጤና ባለሙያዎች የሙያ ሥነ-ምግባር ተላብሰው የሕክምና አገልግሎት ለኅብረተሰቡ መስጠታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- የታካሚዎችን መብት ለማስጠበቅ፣ የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥና የሙያ-ሥነ-ምግባር ጉዳዮች ተገቢ ትኩረት እንዲሰጣቸው መድረክ በማስፈለጉ፣
- በመንግሥትም ሆነ በግል ጤና ተቋማት የሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት ጥራቱን ፣ ደረጃውንና የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር የጠበቀ የታካሚዎችን ፍላጐት ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

  ስለሆነም የአዲስ አበባ የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት በአዋጅ ቁጥር 30/2004 አንቀጽ 8 (11) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት በፀደቀው ደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 40 መሠረት ይህ የአዲስ አበባ ጤና ባለሙያዎች ሥነ-ምግባር ኮሚቴ አፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል 1

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ሙያ የሥነ-ምግባር ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 120/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1) አዋጅ፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 30/2004 ነው፡፡
2) ባለሥልጣን፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነው፡፡
3) ዋና ዳይሬክተር፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ዳይሬክተር ማለት ነው፡፡
4) የጤና ባለሙያ፡- ማለት እውቅና ከተሰጠው የትምህርት ተቋም በጤና የትምህርት ዘርፍ የሰለጠነ እና የጤና አገልግሎት ለመስጠት በአስፈፃሚ አካል የተመዘገበ ሰው ነው
5) የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ፡- ማለት በጤና አገልግሎት ላይ የሚቀርብ ቅሬታዎችን በመቀበል እና በመመርመር ሙያዊ የውሳኔ ሃሳብ ለዋና ዳይሬክተሩ የሚያቀርብ አካል ነው
6) የጤና ተቋም፡- ማለት የጤና ማበልፀግ የበሽታ መከላከል ማከምና መልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ወይም የመድኃኒት ንግድ ሥራን ወይም አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግስት ፣መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ሆኖ ዲያግኖስቲክ ማዕከላትንም ይጨምራል፡፡
7) የጤና አገልግሎት፡- ማለት የጤና ተቋማት የሚሰጥ የጤና ማበልፀግ በሽታ የመከላከል የማዳከምና የማገገም አገልግሎት ነው
8) ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ፡- ማለት ማንኛውም የህብረተሰብ መገልገያ ተቋም ሲሆን ትምህርት ቤት፣ ማረሚያ ቤት፣ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማዕከላት፣ የአሳዳጊ አልባ ህጻናት ማዕከላት፣ መዋዕለ ህፃናት፣ የህጻናት ማቆያ የገበያ ቦታዎች፣

የስፖርት ቦታዎች፣ የመታሻ ማዕከላት፣ የመዝናኛ ማዕከላት ፣ የፀጉር ቤቶችና የውበት ሳሎኖችን ይጨምራል፡፡

9) የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት፡- ማለት በወጣው የጤና ቁጥጥር ደረጃ መሠረት በምግብና፣ በመድኃኒት ወይም ለጤናና ጤና ነክ አገልግሎት ወይም ለኢንዱስትሪዎች የሚሠጥ የሥራ ፈቃድ ነው፡፡

10) የሙያ ሥራ ፈቃድ፡- ማለት የጤና አገልግሎት ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

11) ተገልጋይ፡- ማለት ለራሱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን የጤና አገልግሎት ለማግኘት ሲባል በውል ወይም በሌላ መልኩ ከጤና ባለሙያዎች ጋር የሚፈጠር ታካሚ ወይም ደንበኛ ማለት ነው፡፡

12) አቤቱታ፡- ማለት በጤና ባለሙያ የሚፈጠር የሕክምና አሰጣጥና አሠራር የሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈትን በተመለከተ በታካሚው በጽሑፍ የሚቀርብ አቤቱታ ነው፡፡

13) አቤቱታ አቅራቢ፡- ማለት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የህክምና ቅሬታ አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው ነው

14) አቤቱታ የቀረበበት ሰዉ፡- ማለት የቅሬታ አቤቱታ የቀረበበት የጤና ባለሙያ ወይም የጤና ተቋም ነው

15) ከተማ፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

16) ክንቲባ፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፡፡

17) ገለልተኛ ኮሚቴ፡- ማለት አቤቱታ ለማጣራት ከጤና ባለሙያዎች እና እንደአስፈላጊነቱ ከተለያዩ አካላት የሚቋቋም ገለልተኛ አካል ነው፡፡

18) ሰው፡- ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

19) አስፈጻሚ አካል፡- ማለት የጤና አገልግሎት እና የጤና ባለሙያዎች የመቆጣጠር ስልጣን አግባብነት ባለው ህግ የተሰጠው አካል ነው

20) ተቆጣጣሪ፡- ማለት የጤና ቁጥጥር ተግባራትን እንዲያከናውን አስፈፃሚ አካላት ውስጥ የተመደበ ባለሙያ ነው

21) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አገላለጽ ሁለቱንም ጾታ ይመለከታል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

የዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ፈቃድ በሰጣቸዉና በሚቆጣጠራቸው ጤና ተቋማት ውስጥ በሚሰሩት ጤና ባለሙያዎች ሁሉ ላይ ሙሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 4. የጤና ሙያ የሥነ-ምግባር ኮሚቴ የተቋቋመበት ዓላማ

1) ህብረተሰቡ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ጤና ተቋማት የሚያገኘውን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆንና በሚሰጠው አገልግሎት እንዲረካ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

2) ባለሙያው የሕክምና አሠራር ሂደትና በሀገሪቱ ሕግ፣ የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ባወጣው ሕግ አዋጅ፣ደንብና መመሪያ ከሙያ ሥነ-ምግባር ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማስቻ፣

3) በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈት ወጥ በሆነ አሠራር የእርምት እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

4) ባለሙያው ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት የሙያ ግዴታውን አክብሮ በአግባቡ እንዲወጣ አስፈላጊ በመሆኑ የጤና ሙያ የሥነ-ምግባር ኮሚቴ በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተቋቁሟል፡፡

## 5. መሰረታዊ መርሆች

1. የሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴው በማንኛውም ጊዜ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚውን የማህበረሰብ ክፍል መብትና ጥቅም ማስከበር አለበት፡፡

2. የሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴው የሚከተላቸው የአሰራር ሂደቶች እና የሚሰጣቸው ሙያዊ የውሳኔ ሃሳቦች አግባብነት ያላቸው ህጎች እና የሙያ መርሆዎች የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኮሚቴው ተግባር ሃላፊነትና አደረጃጀት

### 6. የኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነትና

1) የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት ይኖሩታል፡፡
2) በጤና ባለሙያዎች የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚቀርብ የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር አቤቱታ ይቀበላል ይመረምራል መንስኤዎችን አጣርቶ ለዋና ዳይሬክተሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል
3) በጤና ባለሙያ ላይ የቀረበውን አቤቱታ ለማየት የሚያበቃ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ባለሙያው መልሱን እንዲያቀርብና ቀርቦም እንዲያስረዳ በአሥር ቀናት(10) ውስጥ በፀሐፊው በኩል መጥሪያ ይልካል፡፡
4) አስፋጊ ሆኖ ሲያገኘው ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በመመካከር ነፃ የሆነ አጣሪ ወይም መርማሪ አካል በመመደብ የቀረበው አቤቱታ እንዲጣራ ያደርጋል
5) አቤቱታ ባይቀርብም የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ጥሰት በተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው ወይም መረጃ ሲያገኝ ያጣራል
6) ተግባር ሃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ ንዑስ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል
7) አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ ቢያንስ በ20 ቀናት ውስጥ የቀረበበትን አቤቱታ እንዲያስረዳ ያደርጋል፡፡
8) ጉዳዩ ተጣርቶ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ የባለሙያውን የሙያ ሥራ ፈቃድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንዲታገድ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፡፡
9) በተደጋጋሚ የሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈት የሚያደርሱ ጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ማገድ ፣መሠረዝን ጨምሮ በዚህ መመሪያ የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራትና ሌሎች አግባብ ያላቸው የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሣብ ያቀርባል፡፡
10) በተደጋጋሚ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ እና የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መንስኤዎቻቸዉን ይለያል እነዚህን ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመፍታት እንዲቻል የፖሊሲ ሃሳቦችን ማመነጨትና ለዋና ዳይሬክተሩ እና ለሚመለከታቸዉ አካላት ያቀርባል፡፡
11) ኮሚቴው ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚሰጡትን ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 7. የኮሚቴ አደረጃጀት

**ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-**

1/ በዋና ዳይሬክተር አቅራቢነት በክቡር ከንቲባ የሚሰየም ሰብሳቢ

2/ በኮሚቴው የሚመረጥ ም/ሰብሳቢ

3/ የባለሥልጣኑ ተወካይ አባል

4/ በሕግ መሠረት ከተቋቋሙት የጤና ባለሙዎች ማኅበር ከእያንዳንዳቸው እንደአስፈላጊነቱ አንዳንድ አባል

5/ የአዲስ አበባ ምክር ቤት ሁለት አባላት

6/ ከባለሥልጣኑ ሁለት የሕግ ባለሙያ አባል በጠቅላላው 16 አባላት ይኖሩታል፡፡

## 8. የዋና ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ አመዳደብ

1) በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በክቡር ከንቲባ የሚሰየም ከኮሚቴ አባለላት መካከል አንድ ዋና ሰብሳቢ ይመርጣል፡፡

2) ምክትል ሰብሳቢ በመጀመሪያው የኮሚቴ ስብሰባ እለት በኮሚቴው አባላት ይመረጣል፡፡

3) ዋና ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ የሰብሳቢው ስልጣን ኃላፊነት የሚወጣ ጊዜያዊ ሰብሳቢ ከኮሚቴ ውስጥ ሊመረጥ ይችላል፡፡

## 9. የዋና ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1) የኮሚቴው የስብሰባ አጀንዳ ይወሰናል ያቀርባል፡፡

2) የኮሚቴውን ስብሰባ በበላይነት ይመራል፡፡

3) የኮሚቴው አባላት በዚህ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች እና የአሰራር መርሆዎች መሰረት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ይከታተላል፡፡

4) ማንኛውም የኮሚቴ አባል የሥነ-ምግባር ግድፈት አለበት ብሎ ሲያምን ለዋና ዳይሬክተሩ ያሳውቃል፡፡

5) የሚቀርቡ አቤቱታዎች እና የኮሚቴው ስራ በተመለከተ ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር መረጃ ይለዋወጣል፡፡

6) በዋና ዳይሬክተሩ እና በኮሚቴው የሚሰጡ ሌሎች ኃላፊነቶች ይፈፅማል፡፡

## 10. የምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

ዋና ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ሰብሳቢውን ተክቶ ተግባርና ኃላፊነትን ይወጣል፡፡

## 11.የኮሚቴው ፀሃፊ አመዳደብ

ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነት የሚወጡ አንድ የህግ ባለሙያ ይመድባል

## 12.የፀሃፊ ተግባርና ኃላፊነት

የኮሚቴው ጸሃፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) አቤቱታዎችንና ሌላ ተያያዥ ሰነዶችን ይቀበላል በአግባቡ ይይዛል ለኮሚቴው ያቀርባል፤
2) የኮሚቴውን ስብሰባ ቃል ጉባዔ ይይዛል፤
3) በቀረበው የቅሬታ ማመልከቻ ላይ ያልተሟላ ማስረጃ ካለ እንደአስፈላጊነቱ ይሰበስባል እንዲሟሉ ወይም እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
4) የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜ ለኮሚቴው አባላት እና ለሚመለከታቸው አካት ያሳውቃል፤
5) የስብሰባ አጀንዳዎች ቀን እና ተያያዥ ጉዳዮች በተመለከተ ለዋና ሰብሳቢው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
6) በቃለ ጉባዔ የተያዘ የኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ በጽሁፍ በማዘጋጀት ለኮሚቴው እና ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፤
7) የኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ የሚያስቀይር ወይም በውሳኔ ሃሳብ ላይ ተፅኖ ሊኖረው የሚችል እውነታ ወይም ማስረጃ አለ ብሎ ሲምን ለኮሚቴው ወይም ለዋና ሰብሳቢው ያሳውቃል፤
8) ሌሎች በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር እና በኮሚቴው የሚሰጡትን ተግባራት ኃላፊነት ይፈፅማል፡፡

## 13.የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1) የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ በሳምንት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሰብሳቢው ጥሪ ሲደረግለት በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡
2) ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ (50+1) ሆነው ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔው ይሆናል፡፡
3) ኮሚቴው ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ የኮሚቴው ድምጽ ሲሰጥ እኩል ለእኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የኮሚቴው ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፡፡
4) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱ የሆነ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14.የኮሚቴ አባላት ግዴታዎች

ማንኛውም የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር  ኮሚቴ አባል፡-

1) የሙያ ሥነ-ምግባሩን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤
2) የሥነ-ምግባር ግድፈት በኮሚቴው አባል ተፈፅሟል ብሎ ያመነ ማንኛውም የኮሚቴ አባል ይሄንኑ ለዋና  ሰብሳቢ ማሳወቅ አለበት፤
3) በአቢይ እና ንዑስ ኮሚቴ አዘውትሮ መገኘት አለበት፤
4) በማጣርት ሂደት በእጃቸው የሚገኙ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በጥንቃቄና በሚስጥር መያዝ አለበት፤
5) በሚቀርብ ጉዳይ ላይ የጥቅም ግጭት አለ ብሎ ሲያምን ለኮሚቴው አሳውቆ ከማጣራት ሂደት ራሱን የማግለል ግዴታ አለበት፡፡

## 15.በኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

የኮሚቴ አባል ከሚወክለው አካል በፅሁፍ በተረጋገጠ ደበዳቤ አማካይነት የሚሰየም ሲሆን በኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ የሚከተሉትን መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1) የጤና ባለሙያ ከሆነ ህጋዊ የሙያ ስራ ፈቃድ ያለው፤
2) ጥሩ ስነ-ምግባር ያለው፤
3) በስራው ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር ከሚችል ሱስ ነጻ የሆነ፤
4) በህግ መብቱ ያልተገደበ፤
5) ከሙያው ጋር በተያያዘ ወይም ለህሊና ተፃራሪ በሆነ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ያልተባለ፤
6) ህዝብን በቅንነት ለማገልገል ፍላጎት ያለው መሆን አለበት፡፡

## 16.የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን

1) ማንኛውም የኮሚቴው ሰብሳቢ ፀሃፊ እና አባል የሥራ ዘመን ከተመረጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሶስት ዓመት የማይበልጥ ጊዜ ነው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት በኮሚቴ አባልነት ያገለገለ ሰው ከሁለት የአገልግሎት የሥራ ዘመን በላይ መመረጥ አይችልም፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚወከሉትን የህግ ባለሙዎችን አይጨምርም፡፡

## 17.የኮሚቴ አባላት አመራረጥ

የጤና ሙ.ያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ የሚቋቋመው በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 30/2004 አንቀጽ 43 እና ደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 40 መሠረት ከዚህ በታች ከተጠቀሱት የሙ.ያ ማህበራት ይቋቋማል፡፡

1) ከአ/አ/ የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን (1) ሰው፣
2) ከኢትዮጵያ ማህፀንና ፅንስ ሐኪሞች ማህበር (1) ሰው፣
3) ከአጥንት ቀዶ ጥገና ማህበር (1) ሰው፣
4) ከኢትዮጵያ ሰርጂካል ሶሳይቲ (1) ሰው፣
5) ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት (2) ሰው፣
6) ከኢትዮጵያ አኒስቴቶስቶች ማህበር (1) ሰው፣
7) ከኢትዮጵያ ፋርማሲ ማህበር (1) ሰው፣
8) ከኢትዮጵያ ነርሶች ማኅበር (1) ሰው፣
9) ከኢትዮጵያ ህፃናት ሀኪሞች ማህበር (1) ሰው፣
10) ከኢትዮጵያ የወስጥ ደዌ ህክምና ማህበር (1) ሰው፣
11) ከኢትዮጵያ ሚድዋይፎች ማህበር (1) ሰው፣
12) ከኢትዮጵያ ህክምና ማህበር (1) ሰው፣
13) ከኢትዮጵያ የህበረተሰብ ጤና መኮንኖች ማህበር ማህበር (1) ሰው፣
14) ከአ/አ/የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን የህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት (2) ሰው፡፡

## 18.ኮሚቴ የሚፈርስበት ሁኔታዎች

1) ኮሚቴው የተጣለበትን ተግባርና ሃላፊነት አልተወጣም ብሎ ዋና ዳይሬክተሩ ሲያምን አስፈላጊውን የማጣራት ስራ እንዲከናውን ገለልተኛ አካል ሊሰይም ይችላል፡፡
2) ኮሚቴው በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን ተግባር ኃላፊነት በአግባቡ አልተወጣም ብሎ ሲያምን ዋና ዳይሬክተሩ ኮሚቴውን ሊያፈርሰው ይችላል፡፡

## 19. የኮሚቴው ሰብሳቢ ፣ ም/ሰብሳቢና አባል ከስብሰባ የሚነሳበት ወይም ተሳታፊ የማይሆንበት ሁኔታ

1) የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም አባል አቤቱታ አቅራቢ በሚሆንበት ጊዜ፣
2) የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም አባል አቤቱታ በቀረበበት ጊዜ
3) የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም አባል አቤቱታ ከቀረበበት ባለሙ.ያ ጋር የግል ፀብ ወይም የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑን በማስረጃ ሲረጋገጥ ለዚያ ጉዳይ ብቻ ከስብሰባ እንዲነሳ ይደረጋል፣

## 20.ከአባልነት ስለማገድ ወይም ስለማሰናበት

ማንኛውም የኮሚቴ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊታገድ ይችላል፡-

1) የመኖሪያ አድራሻውን ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ መቀየሩን ለባለሥልጣኑ ዳይሬክተር አቅርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ፤
2) የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈት ሲፈፅም ብሎም በማስረጃ ሲረጋገጥ፤
3) በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡ ተግባርና ኃለፊነቶች እንዳይወጣ የሚያደርግ የአካል ወይም የአምሮ ጤና እክል የገጠመው ከሆነ፤
4) በበጀት አመቱ ሶስት ስብሰባዎች ወይም ኮሚቴው ካካሄዳቸው ጠቅላላ ስብሰባዎች ውስት ስድስት ስብሰባዎች ያለበቂ ምክንያት የቀረ እንደሆነ፤
5) ከኮሚቴ አባልነት ለመልቀቅ በራሱ ፍላጎት ያመለከተና ዋና ዳይሬክተሩ ከፈቀደ፤
6) የኮሚቴውን አሰራር እና መልካም ስም ሊያጎድፍ የሚችል ወይም የግል ፍላጎቱን የሚያንፀባርቅ ከሆነ፤
7) ኮሚቴው የተጣለበትን ሃላፊነት እንዳይወጣ እንቅፋት ሆኗል ብሎ ኮሚቴው ካመነ፤
8) የኮሚቴው አባል የወከለው አካል እንዲነሳለት በፅሁፍ ጥያቄ ሲያቀርብ፡፡

## 21.ስለ ንዑስ ኮሚቴዎች

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የተቋቋመው የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ በማቋቋም አንዳንድ ሥራዎችን አጣርቶ የመፍትሔ ሃሣብ እንዲያቀርብለት ማድረግ ይችላል፣
2) ኮሚቴው የራሱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖረዋል፣
3) ኮሚቴው የጤና ሙያ የሥነ-ምግባር ግድፈት እንዲያጣራ የሚቀርብለትን አቤቱታ አጣርቶ ያቀርባል፣
4) ኮሚቴው እንዲያጣራ የቀረበለትን አቤቱታ በተዘጋጀው ቅፅ ሞልቶ ለተከሣሹ ወይም አቤቱታ ለቀረበበት ባለሙያ ጥሪ ያቀርባል፣ አስፈላጊውን ማስረጃ በማሰባሰብ አጣርቶ ለጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ያቀርባል፣
5) ከጤና ተቆታጣሪ ጋር በመሆን አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን፣ የመጽሐፍትን ቅጂ፣ ሌሎች አስፈላጊ የሚላቸውን በመፈተሽና በማረጋገጥ ማስረጃ ይይዛል፡፡
6) ንዑስ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ አቤቱታ አቀረረብ ምርመራና የውሳኔ ሃሳብ አሰታጥ ሥነ-ሥርዓት

### 22.የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

1) አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው ጉዳት በደረሰበት ግለሰብ፣ በአሳዳጊው፣ በሕጋዊ ተወካዩ ወይም ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል ህጋዊ አካል ሊሆን ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንድ(1) መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ የሥነ-ምግባር ግድፈት ከተፈፀመ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3) አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በጽሁፍ ሆኖ አቤቱታውን ዝርዝር ሁኔታ፣ በባለሙያው ተፈጸመ የተባለው ግድፈት፣ የባለሙያው ሙሉ ስምና አድራሻ እና የአቤቱታ አቅራቢውን ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡
4) አቤቱታ አቅራቢው በኮሚቴው ጸሃፊ የሚቀርብለትን ቅጽ በአግባቡ መሙላት አለበት፡
5) አቤቱታ አቅራቢው የመታወቂያ ደብተሩን ኮፒ በአባሪነት ማያያዝ አለበት፡፡
6) አቤቱታ አቅራቢው ምስክሮች ወይም አቤቱታውን የሚያጠናክሩለትን ማስረጃዎች ካሉት የምስክሮችን ስም ዝርዝር እና አድራሻ እንዲሁም የማስረጃ ሰነዱን ከአቤቱታ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
7) የኮሚቴው ጸሃፊ አቤቱታ ለቀረበበት ሰው የቀረበበትን የአቤቱታ ዝርዝር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

### 23.የቅድመ ማጣራት ሂደት

1) ኮሚቴው በዚህ መመሪያ መሰረት በቀረበ አቤቱታ ላይ የማጣራት ስራ ለማካሄድ የቀረበው ማስረጃ በቂ ሆኖ ካላገኘው ከተከሳሽ ወይም ከሌላ ማንኛውም አካል ማስረጃ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚሰበሰብ ማስረጃ መሰረት ግድፈት ተፈጽሟል የሚያስብል ምክንያት ከተገኘ ኮሚቴው ምርመራ ያካሂዳል፡፡
3) ኮሚቴው የመጨረሻውን የውሳኔ ሃሳብ ከመስጠቱ በፊት የቀረበለትን አቤቱታ የጉዳዩን ባህሪ መሰረት በማድረግ ባለሙያው የጤና አገልግሎት እንዳይሰጥ የሙያ ፈቃዱ በጊዜአዊነት እንዲታገድ ሊያደርግ ወይም የተወሰኑ የሙያ ተግባራትን

ብቻ እንዲያከናውን ትእዛዝ ሊሰጥ ወይም ይህንን ለሚመለከተው አካል ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የተላለፈው የእግድ ወይም የክልከላ ትእዛዝ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ከ90 ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

5) አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ ላይ ኮሚቴው ምንም አይነት አሳማኝ ማስረጃ ካላገኘበት እገዳውን ወይም ክልከላውን ወዲያውኑ ማንሳት አለበት፡፡

24.ክስን ስለመከላከል እና እንዲነሳ ስለመጠየቅ

1) አቤቱታ እንደቀረበበት ያወቀ እና ቀርቦ እንዲከላከል በኮሚቴው ጸሃፊ በኩል መልእክት የተላለፈለት ባለሙያ መጥሪያው በደረሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ እንደሁኔታው ምስክሮች እና ማስረጃዎች ካሉት ይህንኑ በማካተት የመከላከያ መልሱን ማቅረብ አለበት፡፡

2) የቀረበው የመከላከያ መልስ በዋናነት የአቤቱታ አቅራቢውንና አቤቱታ የቀረበበትን ሰው ስምና ሙሉ አድራሻ፣ ለእያንዳንዱ የክስ ዝርዝር የቀረበ የመከላከያ መልስ ሙሉ መግለጫ እንዲሁም እንደሁኔታው የምስክሮችን ሙሉ ስምና አድራሻ እና የማስረጃ ሰነዶችን ኮፒ ማያያዝ አለበት፡፡

3) ተከሳሽ ያቀረበውን የመከላከያ መልስ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጠዋል፡፡

4) አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ በቀረበበበት እያንዳንዱ የክስ ፍሬ ነገር ላይ በቀጥታ ወይም  የመከላከያ መልስ ካላቀረበ መከላከያ መልስ ያልቀረበበት ፍሬ ነገርን በሚመለከት እንዳልተከላከለ ተቆጥሮ ክሱን እንደተቀበለው ይቆጠራል፡፡

5) አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ በቀረበው ክስ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ክሱ እንዲነሳለት መጠየቅ የሚችለው የቀረበው ክስ፡-

   ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት ለኮሚቴው ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት ውጭ ከሆነ፤

   ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 (2) መሰረት የጊዜ ገደቡ ያለፈ ከሆነ፤ ወይም

   ሐ) ከዚህ በፊት በዚህ ኮሚቴ ወይም በሌላ ህጋዊ አካል ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ነው፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት መጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያ ከቀረበ ኮሚቴው የክሱን ፍሬ ነገር ከመመልከቱ በፊት በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

7) ኮሚቴው የክሱን ፍሬ ነገር መመልከት ከጀመረ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም አይነት የመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡

**25.አቤቱታ ወይም የመከላከያ መልስ ስለማሻሻል**

1) አቤቱታን ወይም የመከላከያ መልስ ሊሻሻል የሚችለው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት እና አግባብነቱ በኮሚቴው ታይቶ ከታመነበት ብቻ ነው፡፡
2) ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ ወይም የመከላከያ መልስ መሻሻል አለበት ብሎ ሲያምን ይኸው እንዲሻሻል በማንኛውም ጊዜ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3) የቀረበው አቤቱታ ወይም የመከላከያ መልስ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከተሻሻለ አንደኛው ተከራከሪ ወገን እንደሁኔታው ሊያሻሻል ይችላል፡፡

**26.አቤቱታ ስለማንሳት**

1) አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታ ለማንሳት የሚችለው፡-
   ሀ) ይኸው ጥያቄ በጽሁፍ ከቀረበ እና
   ለ) ጉዳዩ የማህበረሰቡን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑ በኮሚቴው ከታመነ እና
   ሐ) ጥያቄው የቀረበው ኮሚቴው የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከሆነ
   ብቻ ነው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተነሳ ማንኛውም አቤቱታ በድጋሚ ለኮሚቴው ሊቀርብ አይችልም፡፡

**27.መጥሪያ ስለመላክ**

1) ኮሚቴው ጉዳዩን ለመስማት ከቀጠረበት አስር(10) ቀናት በፊት የኮሚቴው ጸሃፊ የአቤቱታ ኮፒ አቤቱታ ለቀረበበት ባለሙያ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡
2) የአቤቱታ ኮፒው ለባለሙያው በቀጥታ ሊሰጥ፣ ወይም ባለሙያው መጥቶ እንዲወስድ ወይም ባለሙያው ካልተገኘ ለሚሰራበት ተቋም ሊሰጥ ይችላል፡፡
3) አቤቱታ ያቀረበው አካል ወይም አቤቱታ ለቀረበበት ባለሙያ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ እንዲገኝ አስፈላጊ ነው ብሎ ኮሚቴው ካመነ በጸሃፊው አማካኝነት የስብሰባው ቀን፣ ሰዓትና ቦታን በመጥቀስ እንዲቀርብ ጥሪ ይደረግለታል፡፡

**28.አቤቱታ ስለመመርመር**

1) አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ እንዲከላከል ጥሪ ከተደረገለት ቀን ጀምሮ ጉዳዩ መታየት ይጀምራል፡፡

2) ኮሚቴው አቤቱታ አቅራቢውን ወይም አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ ሁለቱም ባለቡት ጉዳዩን ማየት ይችላል፡፡

3) የቀረበውን አቤቱታ ወይም የመከላከያ ማስረጃ መብራራት አለበት ብሎ ኮሚቴው ካመነ የመጨረሻ የውሳኔ ሃሣብ ለባለሥልጣኑ ዳይሬክተር ከማቅረቡ በፊት ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4) ኮሚቴው ተከሳሹ ያቀረበውን ማስረጃ አይቶ ካረጋገጠ በኃላ የውሣኔ ሃሣብ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

## 29.ጉዳዩ በሚታይበት እለት አቤቱ አቅራቢው ወይም አቤቱታ የቀረበበት አካል መቅረት

1) ተከሳሹ ጉዳዩ በመሚታይበት ጊዜ እንዲቀርብ በኮሚቴው ተጠርቶ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኮሚቴው የአቤቱታ አቅራቢውን ማስረጃዎች እና የምስክር ቃል ሰምቶ በተሰጠው ማስረጃ መሰረት የውሳኔ ሃሳብ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2) ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ መገኘት እንዳለበት የተነገረው ተከሳሽ ሳይገኝ የቀረበትን አሳማኝ ምክንያት በአስር(10) ቀናት ውስጥ ለኮሚቴው ጸሃፊ ካቀረበ እና ኮሚቴው ካመነበት እንደገና ሊታይ ይችላል፡፡

3) አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩ በመሚታይበት ጊዜ ላይ መገኘት እንዳለበት ተነግሮት ሳይቀርብ ሲቀር ጉዳዩ የማህበረሰቡን ጥቅም የማይጎዳ ከሆነ ኮሚቴው የቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲሆን ሊወስን ይችላል፡፡

4) ጉዳዩ በመሚታይበት ጊዜ መገኘት እንዳለበት የተነገረው አቤቱታ አቅራቢ ሳይገኝ ቀርቶ የቀረበትን አሳማኝ ምክንያት ከቀረበት አስር(10) ቀናት ውስጥ ለኮሚቴው ጸሃፊ አቅርቦ ኮሚቴው ካመነበት እንደገና ሊታይ ይችላል፡፡

## 30.ስለ ምስክሮች

1) ኮሚቴው ምሥክሮች ቀርበው የምሥክር ቃላቸውን እንዲሰጡ በፀሐፊው በኩል ጥሪ ያደርጋል፡፡

2) ኮሚቴው ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የምሥክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ጥሪ የተደረግላቸው ምሥክሮች ተራ በተራ ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ ይደርጋል፡፡

3) አቤቱታ አቅራቢው ወይም የሥነ-ምግባር ግድፈት አድርሷል ተብሎ የተጠረጠረ ባለሙያ ለምሥክርነት ወይም ለመከላከያነት ለሚቆጥራቸው ምሥክሮች የጥሪውን ወረቀት የሚያደርሰው እራሱ ነው፡፡

4) የምሥክር ቃሉን እንዲሰጥ የጥሪ ወረቀት ደርሶት ለመቅረብ ፈቃደኛ ያልሆነ ምሥክር በሕግ አካል ቀርቦ የምሥክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

5) ለምሥክርነት የተጠራው ማንኛውም ሰው ለኮሚቴው ካልሆነ በስተቀር ለምሥክርነት ስለተጠራበት ጉዳይ ለማንም እንዲገልጽ አይገደድም፡፡

6) ለምሥክርነት የተጠራ መስካሪ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃለ-መሐላ ይፈጽማል፡፡

7) ምሥክር እንዲሆን የተጠራው ሰው ስለተጠራበት ጉዳይ የምሥክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት በኮሚቴው ይገለጽለታል፡፡ አቤቱታ አቅራቢም ሆነ የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈት ማድረሱ ክስ የቀረበበት ሰው መስቀለኛ ጥያቄ ለመስካሪው ማቅረብ ይችላሉ፡፡

8) የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ የተጠራ ምስክር የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በጽሁፍ መስፈር እና መፈረም አለበት፡፡

## 31.ሌሎች ማስረጃዎችን ስለመቀበልና ስለመመርመር

1) ኮሚቴው ለቀረበው አቤቱታ አስፈላጊ ይሆናል ብሎ ያመነበትን ማስረጃ ሁሉ ሊቀበል ይችላል፡፡

2) ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ የውሣኔ ሃሣብ ለማቅረብ ተጨማሪ ማረጋገጫና ምሥክር ያስፈልጋል ብሎ በጉዳዩ ካመነ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡

3) ተቆጣጣሪ ባለሙያው ተመዝግበው የሚያዙ የጤና መዛግብት፣ የሕክምና መሣሪያዎች ፣ ሌሎችም ቁሳቁሶች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ጤና ተቋማት ገብቶ ማጣራትና በመያዝ ለኮሚቴው ማቅረብ ይችላል፡፡

4) የጤና መረጃን፣የሕክምና መሳሪያ ወይም ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎችን የሚይዝ ማንኛውም የጤና ተቋም ኮሚቴው በባለስልጣኑ በሚወክለው አካል ጉዳዩን ለማጣራት አስፈላሂውን ምርመራ እንዲያደርግ መፍቀድ ይኖርበታል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ማጣራትና ምርመራ የሚፈጸመው በመደበኛ የመንግሥት የሥራ ሰዓት ይሆናል፡፡

## 32. የውሳኔ ሃሳብ እና አፈጻጸም

1) ኮሚቴው የመስማት ሂደቱን ካጠናቀቀ በኋላ ቢያንስ በሚቀጥለው የስብሰባ ጊዜ የውሳኔ ሃሳብ ማስተላለፍ አለበት፡፡

2) የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ በተሰጠ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የኮሚቴው ጸሃፊ ውሳኔዎችን በጽሁፍ አዘጋጅቶ እንዲፈረም ያቀርባል፡፡

3) የኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ በተፈረመ በሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ መፈረም አለበት፡፡

4) የውሳኔ ሃሳቡ በባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ከጸደቀ በኋላ ውሳኔው በተከሳሹ፣ በቀጣሪው ተቋም፣ በፍቃድ ሰጭ አካል ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው አካላት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

5) ውሳኔው በዚህ መመሪያ መሰረት በህጋዊ አካል ካልታገደ በስተቀር በተከሳሽ ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ ወይም ተፈጻሚ ካልሆነ በባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ወይም ጉዳዩን አግባብ ላለው የሕግ አስፈጻሚ አካል ማስተላለፍ ይችላል፡፡

## 33.አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1) የተፈጸመውን የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈት ክብደት መሰረት በማድረግ ኮሚቴው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡-

   ሀ. የቃል ማስጠንቀቂያ፣

   ለ. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣

   ሐ. ሥልጠና ተሰጥቶት እራሱን እንዲያሻሽል ማድረግ፣

   መ. ልምድ ባለው ባለሙያ ክትትልና ቁጥጥረ ስር ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ እንዲሰራ ማድረግ፤

   ሠ. ጥፋተኛ ከተባለበት ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሙያ ስራዎችን እንዳይሰራ ማገድ፤

   ረ. የሙያ ፈቃዱን ለተወሰነ ጊዜ ማገድ ፣

   ሰ. የሙያ ፈቃዱን መሠረዝ፡፡

   ሸ. አግባብነት ያላቸው ሌሎች እርምጃዎች መዉሰድ

2) የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ማድረሱ የተረጋገጠበት የጤና ባለሙያ የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ማድረሱን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል እና ለሚሰራበት ተቋም ማሳውቅ

3) በጉዳዩ ላይ ባለሙያው የሚሰራበት የጤና ተቋም የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈቱ አስተዋጽኦ ካለው ኮሚቴው ይኼንኑ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ እና አግባብ ያለው እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ከተራ ቁጥር “ሀ” እስከ “መ” የተዘረዘሩት ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተብለው ይመደባሉ፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ከተራ ቁጥር “ሠ” እስከ “ሰ” የተዘረዘሩት ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተብለው ይመደባሉ፡፡
6) ኮሚቴው ቅሬታ የቀረበበት የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ክብደት፣ ባህሪ፣ በጤና ላይ ያደረሰውን ጉዳት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀላል ወይም በከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ ቅጣት ይወስናል፡፡
7) በዚህ አንቀጽ መሰረት ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰደው የተፈጸመው የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈት ከፍተኛ የጤና ችግር ሊያስከትል የሚችል ሲሆን ወይም በሰው ላይ ሞት የሚያስከትል እና ወይም በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ከሆነ ነው፡፡
8) በዚህ አንቀጽ መሰረት ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰደው የተፈጸመው የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት አነስተኛ ከሆነ ወይም በህይወት ወይም በጤና ላይ ምንም አይነት ጉዳት የማያስከትል ሲሆን ነው፡፡
9) ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስከትል የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ግድፈት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ የፈጸመ ባለሙያ በከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ ይቀጣል፡፡

## 34.ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃዎች

ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስቀጡ ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) በሙያ ፈቃድ ላይ የተቀመጠውን የስራ ወሰን ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ ተላልፎ ሲገኝ፤
2) የሙያ ስያሜን፣ ማእረግን እና ውክልናን አለአግባብ መጠቀም፤
3) ለፈቃድ ሰጭው አካል አስፈላጊውን መረጃ አለመስጠት፤
4) በቂ የሕክምና ምርመራን ሳያደርጉ የሕክምና ውጤትን መስጠት፤
5) ከአንድ ጤና ባለሙያ የሚጠበቀውን ሕግና ደንብ በማንኛውም ሁኔታ ሳይጠብቁ መቅረት፤
6) ለህመምተኛው የተሰጠውን የሕክምና መረጃ በአግባቡ ሳይመዘግቡ ሲቀሩ፤
7) ሌሎች ተመሳሳይ| የሆኑ የስነ ምግባር መተላለፎችን ሲፈጸሙ፤
8) የሥራ ሰዓት አክብሮ ለታካሚ ሕክምና ያለመስጠት (አርፍዶ ሥራ መግባትና ቀድሞ መውጣት) ያለ በቂ ምክንያት ከስራ ምቅረት ናቸው፡፡

## 35.ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎች

ከባድ የአስተዳደራዊ እርምጃዎች የሚወሰዱት፡-

1) ቀላል ጥፋቶችን በተደጋጋሚ ሲፈጽሙ፤
2) ለኮሚቴ የምርመራ ሂደት ትብብር አለማድረግ፤
3) በሙያዊ እንቅስቀሴ ላይ ሀቀኝነት ሲጎድል እና የማታለል ስራ ሲፈጽሙ፤
4) በሽተኞችን ሲያመናጭቁ፤
5) ሕክምናው የተከናዎነው የታካሚውን ፈቃድ ሳያገኙ ከሆነ፤
6) ከበሽተኞች ጋር አላስፈላጊ የሆነ ግንኙነት (የፍቀቅር ወይም የጥቅም)፤
7) ወንጀል ሲፈጽሙ (የጾታ ትንኮሳ አስገድዶ መድፈር……)፤
8) በግዴለሽነት በሽተኛው ላይ አእምሮአዊ እና አካላዊ ጉዳት ሲያደርሱ፤
9) በኮሚቴው የተሰጠውን ትእዛዝና ውሳኔ በመተላለፍ ሲሰራ ከተገኘ፣ እና
10) አልኮል ወይም አደንአዛዥ እጽ ተጠቅሞ የሕክምና አገልግሎት መስጠት
11) ለጤና አገልግሎት ተጠቃሚው አስፈላጊ ያልሆነ ሕክምና ማዘዝ ወይም መተግበር፤
12) የበሽተኛውን መረጃ ያለበሽተኛው ወይም ተወካዩ ፈቃድ ለሁለተኛ ወገን አሳልፎ ከሰጠ፤
13) የህክምና ፋይል መቀየር፤መደለዝ መሰረዝ፤
14) የህክምና ፋይል ህጋዊ አካል ሲፈልግ አለማቅረብ እና መደበቅ፤
15) ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ጥፋቶች ሲፈጸሙ፤

## 36.በባለሙያው ላይ የተወሰደው የሥነ-ምግባር አስተዳደራዊ እርምጃ በሪከርድነት የሚጠቀስበት ጊዜ

1) ቀላል የዲሲፕሊን እርምት እርምጃ የተወሰደበት ባለሙያ እስከ 2 ዓመት
2) ከባድ የዲሲፕሊን እርምት እርምጃ የተወሰደበት ባለሙያ እስከ 4 ዓመት ድረስ በሪከርድነት ይጠቀስበታል፡፡

## 37.ይግባኝ

1) በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ ኮሚቴው የሚሰጠቀው የውሳኔ ሃሳብ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ውሳኔ የተላለፈበት አካል በውሳኔው ላይ የሕግ ወይም የሥነ ሥርዓት ጥሰት ተፈጽሟል ብሎ ካመነ ውሳኔው በተላለፈ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት ይግባኙን ከተቀበለው በፍርድ ቤቱ ግኝት መሰረት ጉዳየዩ እንደገና በኮሚቴው እንዲታይ ይደረጋል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኝ ለጠየቀው ወገን የውሣኔው ግልባጭ በ10 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ይሰጠዋል፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት እስከ 15 ቀን ሊቆይ ይችላል፡፡

5) ከሙያ ፈቃድ መታገድ ጋር የተያያዘ ይግባኝ ከአንድ(1) ወር በኃላ ይግባኝ ሊባልለት አይችልም፡፡

6) ከሙያ ፈቃድ መሠረዝ ጋር የተያያዘ ይግባኝ ከሶስት(3) ወር በኃላ ይግባኝ ሊባልለት አይችልም

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በጊዜው ይግባኝ ለማቅረብ ያልተቻለበትን ምክንያት በዝርዝር የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ተያይዞ ከቀረበ ይግባኙ ሊታይ ይችላል፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የቀረበው ይግባኝ ባዩ ማመልከቻውን አቅርቦ በ10 ቀናት ውስጥ አቅርቦ የይግባኙን ግልባጭ መውሰድ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## የተለያዩ ድንጋጌዎች

**38.የኮሚቴ አባላት ክፍያን በሚመለከት**

የኮሚቴው አባላት ክፍያ የሚወሰነው የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለዚህ ዓላማ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**39.ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**40.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው ከመጋቢት 2007 ዓ.ም ጀምሮ ይሆናል፡፡

ዋና ዳይሬክተር

የአዲስ አበባ ከተማ የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ

አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን